# 6. እዉነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት?

### በዚህ ትምህርት ዉስጥ የሚከተለትን ይማራሉ

ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነዉ?
እዉነተኛ ቤተ ክርስቲያን ምን ታደርጋለች?
የቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ለምን አስፈለገ?
በቤተ ክርቲያን ያለዉ እንቅስቃሴ ምንድን ነዉ?

## ክፍል 1

## ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?

ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ብዙ ትርጉሞች አሉት።

**ለክርስቶስ የተለዩ ሰዎች**

ኢየሱስ ሲናገር «ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ» አለ /ማቴ 16፡18/። እዚህ ላይ የተጠቀመበት ቃል ትርጉሙ ተለይተው የወጡ ማለት ነው። እንድንከተለው ጠርቶናል። አሮጌውን የኃጢአት ህይወት በመተው ኢየሱስን መሪያቸው አድርገው እውቅና በመስጠት ተለይተው የወጡ አካል ብልቶች እንሆናለን። እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ይህች ናት። አካሎችን ሁሉ የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከእነዚህም አብዛኞቹ በመንግስተ ሰማይ ይገኛሉ።

**ቆላስያስ 1፡18** እርሱ አካሉ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው።

**ሮሜ 12፡5** እንዲሁም እኛ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን። እያንዳንዳችንም የሌላው ብልት ነን።

**አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን**

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ይደረግ እንደነበረው ሁሉ በክርስቶስ አንድ ዓይነት እምነት ያላቸው የአንድ አካባቢ ሰዎች በየጊዜው እየተገናኙ አብረው ያመልኩታል። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አቋቁመው አብረው ለጌታ ይሰራሉ።

**ማቴ 18፡20** ሁለት ወይም ሶስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት መካከል በዚያ እገኛለሁና።

**ቆላ 4፡ 15** በሎዶቅያ ላሉት ወንድሞች ቤቷም ላለች ቤተክርስቲያን ሰላም አቅርቡልኝ፡፡

**አገር አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እምነት**

ቤተ እምነት ማለት በርካታ አጥቢያ ቤተክርስቲያኖችን የያዘ ድርጅት ነው፡፡ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር የሚረዳዱ እና በተናጥል ከመስራት ይልቅ አብረው በመሆን ለጌታ የበለጠ መስራት የሚችሉ ናቸው፡፡ ስነ ጽሑፎችን ያትማሉ፡፡ አገልጋዮችን ያሰለጥናሉ፡፡ አዳዲስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን ይከፍታሉ፡፡ እንዲሁም ትምህርት ቤቶችን እና የወላጅ አልባ ልጆች ማሳደጊያ ቦታዎችን ያንቀሳቅሳሉ፡፡

የአገር አቀፉ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እምነት መሪዎች ሐዋሪያው ጳውሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ያደርግ እንደነበረው ሁሉ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች በችግራቸው ይረዷቸዋል፡፡

**ሐዋሪያት ሥራ 15፡6፣ 23፣41** ሐዋሪያትና ሽማግሌዎችም ይህንኑ ጉዳይ ለማጤን ተሰባሰቡ፡፡ በእነርሱም እጅ.. ደብዳቤ ላኩ. . . አብያተ ክርስቲያናትንም እያበረታቱ በሶሪያና በኪልቅያ በኩል አለፉ፡፡

ስለትክክለኛ የአምልኮ ስርዓት፣ ስለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር እና ስላንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ትርጉም አሰጣጥ ላይ በሚፈጠሩ ልዩነቶች ምክንያት የተለያዩ ቤተ እምነቶች ተፈጥረዋል፡፡ ይሁን እንጂ በርካታ ቤተ እምነቶች በዋና ዋና ነጥቦች ላይ በመስማማት በአገልግሎትም ሆነ በአምልኮ ይተባበራሉ፡፡

እንዲሁም ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድ ላይ የሚሰበሰብበት ሕንጻ ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ ትልቅ ይሁን ትንሽ በጣም በጌጣጌጦች ያሸበረቀ ወይም ምንም የሌለው ሊሆን ይችላል፡፡ ዋናው ቁም ነገር የእግዚአብሔር በቦታው መገኘው እንጂ የአዳራሹ ይዘት አይደለም፡፡

## የሚከተሉትን ይስሩ

እያንዳንዱን ዐረፍተ ነገር በትክክል የሚያጠናቅቀውን ሐረግ ያስምሩበት፡፡

- ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ ብሎ በተናገረ ጊዜ ቤተክርስቲያን ለማለት የተጠቀመበት ቃል ትርጉሙ
  ሀ. አገር አቀፋዊ የሆነ የመሪዎች እና የአገልጋዮች ድርጅት ነው፡፡
  ለ. ከዓለም ተለይተው የወጡ ሰዎች ስብስብ ማለት ነው፡፡
  ሐ. ለፀሎትና ለአምልኮ የተለየ ስፍራ ማለት ነዉ፡፡

  መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን አካል እንደሆነች ሲናገር የሚሰጠዉ ትኩረት
  ሀ የተለያዩ ብልቶች ክርስቶስን ራስ አድርገዉ በአንድነት ስለመኖራቸዉ ነዉ፡፡
  ለ
  ልጆችን የሚያስተምሩ እና ወላጅ የሌላቸውን የሚረዱ ሰዎች ስብስብ ነው፡፡

# ክፍል 2

## እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ምን ታደርጋለች?

በዚህና በክፍል ሶስት ዉስጥ ቤተ ክርስቲያን የሚለዉ ቃል የሚያመለክተው በአጥቢያ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የምትንቀሳቀሰዋን የክርስቶስ አካል ነው።

## እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ትወዳለች ለእርሱም ትኖራለች።

እግዚአብሔር ፍጹም በሆነ ፍቅር እንድንወደው ይፈልጋል። የፈጠረን ልጆቹ እንድንሆን በፍቅሩ ደስ እንዲለንና እንድንወደው ነው። ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር የምትገናኝ በአምልኮ ነው። በግል እና በሕብረት ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር በጸሎት፣ በውዳሴ፣ በዝማሬ፣ በመስጠት፣ በማገልገል እና ለትዕዛዙ ታዛዦች በመሆን ይገልጻሉ።

## እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ስለ ኢየሱስ ለዓለም ትመሰክራለች።

እያንዳንዱ ክርስቲያን ለቤተሰቦቹ እና ለጓደኞቹ እንዴት ሊድኑ እንደሚችሉ መናገር አለበት። የወንጌል መልዕክት በዓለም ሁሉ ለማዳረስ እንድንችል መንፈስ ቅዱስ ያግዛል።

## ይሚከተሉትን ጥቅሶች በቃልዎ ይያዙ

***ማር 5፡19*** *«ወደ ቤትህ ሂድ ለዘመዶችህም ጌታ ምን ያህል ታላቅ ነገር እንዳደረገልህና ያሳየህን ምሕረት ንገራቸዉ»*

***ማር 16፡15*** *«ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ»*

***ሐዋ ፲፡8*** *«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኃይል ትቀበላላችሁ እስከ ምድር ዳርቻ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ»*

## እዉነተኛ ቤተ፡ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል ታስተምራለች

ቤተ ክርስቲያን በሚቻለዉ መንገድ ሁሉ ለምዕመናን የእግዚአብሔርን ቃል እዉነት በማስተማር የኢየሱስ ተከታዮች ታደርጋለች

**ማቴ 28:19-20** «ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸዉ ደቀመዛሙርቴ አድርጉአቸዉ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸዉ»

## ቤተ ክርስቲያን ለምዕመናን ትጠነቀቃለች

ቤተ ክርስቲያን መደበኛ የአምልኮ ጊዜ በማዘጋጀት የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት በማካሄድ ሕብረት በመፍጠርና በማገልገል መንፈሳዊ እድገት እንዲኖር ታደርጋለች። ቤተ ክርስቲያን ችግር ላለባቸዉ እርዳታ ታደርጋለች የምክር አገልግሎትም ትሰጣለች።

# ክፍል 3

## ቤተ ክርስቲያን ስለሚያስፈልግዎ

በመንፈሳዊ ነገር የሚረዱና የሚያስተምሩ ሰዎችን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስቀምጧል። በዚህ መንገድ መንፈሳዊ ፍላጎቶችዎን ያሟላል።

**ኤፌ 4:11:12** «አንዳንዶች ሐዋሪያት አንዳንዶች ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች ሌሎቹ ደግሞ እረኞች አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው። ይህውም የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ስራ ለማዘጋጀት።»

ወደ ቤተ ክርስቲያን መቀላቀል ያለብዎ በገንዘብ፣ በምግብ፣ ወይም በሌሎች ቁሳቁሳዊ ነገሮች ርዳታ አገኛለሁ በሚል ዓላማ መሆን የለበትም። በመጀመሪያ እግዚአብሔርን በሕይወትዎ ሲያስቀድሙ የሚያስፈልጉዎን ነገሮች ደግሞ እርሱ ያሟላል።

## ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ስለሆኑ

እያንዳንዱ የአካሉ ክፍል የሚሰራው ስራ አለ። የክርስቶስ አካል ብልት እንደመሆንዎ መጠን የሚሰሩት ስራ አለ። ጣት በራሱ ብቻውን ጠቃሚ መሆን ካለበት ከእጅ ጋር መገናኘት አለበት። እንዲሁ ሁሉ እርስዎም በህይወትዎ ለእግዚአብሔር

የመጀመሪያውን ስፍራ በመስጠት ሌሎችን ለመርዳት እግዚአብሔር እንዲጠቀምብዎ ይፍቀዱለት::

**ሮሜ 12:4፣6** «እያንዳንዳችን በአንዱ አካላችን ብዙ ብልቶች እንዳሉን እንዚህም ብልቶች አንድ አይነት ተግባር እንደሌላቸው ሁሉ እንደተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች አሉን::»

## እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ የሚያገለግሉት በቤተክርስቲያን ውስጥ ስለሆነ ነዉ::

የውኃ ጥምቀት ስርዓትን በመፈፀም ቤተ ክርስቲያንን መቀላቀልዎ ለሌሎች ጥሩ ምስክር መሆንና ለእግዚአብሔርም መስጠትና መታዘዝ ነው:: ካለዎ በመስጠትም እግዚአብሔርን ያገለግላሉ:: ይህን በሁሉም ቦታዎች የሚሰራ ወንጌል ለማዳረስ ገንዘባቸዉ በመስጠት የሚያገለግሉ ብዙ ናቸዉ:: እርስዎ ለወንጌል ስራ ገንዘብ የሰጠ ሰው ስለነበረ ወንጌልን ሊሰሙ ችለዋል:: እርስዎም በመስጠትዎ ምክንያት ሌሎች ወንጌልን ይሰማሉ፣ ይድናሉ::

**2 ቆሮ 9:6:7** «ይህን አስታውሱ ጥቂት የዘራ ቂት ያጨዳል ብዙ የሰራ ብዙ ያጨዳል:: እያንዳንዱ ሰው በቅሬታ ወይም በግዴታ ሳይሆን በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ ምክንያቱም እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው ይወዳል::»

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ የአገልግሎት ዕድሎች አሉ:: መጸለይ፣ መመስከር፣ ትራክቶችን ማሰራጨት፣ መዘመር፣ ማስተማር፣ መስበክ እና ሌሎችን ወደ ቤተ ክረስቲያን መውሰድ ጥቂቶች ናቸው:: በታማኝነት ቤተ ክርስቲያን መከታተልዎ እንኳ እግዚአብሔርን የሚያስደስትና ሌሎችንም የሚያበረታታ ነው::

**ዕብ 10:25** «አንዳንዶች ማድረጉን እንደ ተውት መሰብሰባችንን አንተው ይልቁንም ቀኑ እየተቃረበ መምጣቱን ስታዩ እርስ በርሳችን እንበረታታ::»

### የሚከተሉትን ይስሩ

አቶ ተስፋሁን በቤቱ ሆኖ መጸለይና የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ስለሚችል ቤተ ክርስቲያን መሄድ አያስፈልገኝም ብሎ ያምናል:: በአመለካከቱ የተሳሳተ መሆኑን እንዲረዳ በምን መልኩ ሊያስረዱት ይችላሉ? የተሻለ መልስ በሆነው ምክር ላይ ያስምሩበት::

- አያስፈልጉኝም ብሎ ቢያስብም እንኳ ጓደኞች እንዲሚያስፈልጉት ማስረዳት::
- ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የመገናኘቱ ዓላማ ምን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ማስረዳት::
- ሌሎች ክርስቲያኖች ገንዘብ ሲቸግራቸው ሊረዱት እንደሚችሉ መንገር::

# ክፍል 4

## በቤተ ክርስቲያን ላይ እየሆነ ያለዉ ምንድን ነዉ?

### የሁለት ሺህ አመታት ተጋድሎ

ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ከመሰረታት ጀምሮ ሰይጣን ውጊያ እያካሄደባት ይገኛል፡፡ ቤተክርስቲያን ነፍሳትን ከሰይጣን ውሸትና ሽንገላ ለማዳን በውጊያ ላይ ናት፡፡

**ኤፌሶን 6:12** «ተጋድሎአችን ከስጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከዚህ ዓለም ገዢዎች ፣ ከስልጣናት ከኃይላት እንዲሁም ከሰማያዊ ስፍራ ካሉ ከርኩሳን መናፍስት ሰራዎት ጋር ነው፡፡»
**1 ጴጥ 5:8** «ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፣ ንቁም ጠላታችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሳ አንበሳ ወዲህ ወዲያ ይዞራል»፡፡

### የሰይጣን ስልት እና መሳሪያዎች

ሰይጣን ቤተ ክርስቲያንን ለማሸነፍና ክርስቲያኖችን ከክርስቶስ ለመለየት ይሞክራል፡፡ ዋና ዋና ስልቶቹ ስደት፣ ማታለልና ፈተና ናቸው፡፡
ክርስቲያኖችን ለመግደል እና ለማሳደድ ሰዎችን ይጠቀማል፡፡ የሐሰት አስተማሪዎችን ወደ ቤተ ክርስተያን ይልካል፡፡ ደካማ እና ኃይል የሌላቸው እንዲሆኑ በኃጢአት ይፈትናቸዋል፡፡ እግዚአብሔርን እንዲጠራጠሩ ያደርጋቸዋል፡፡

### የቤተ ክርስቲያን ስልት እና መሳሪያዎች

የእኛ መከላከያ የሰራዊት አለቃ ከሆነው ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ተጣብቆ መኖር ነው፡፡ ዋና ዋና መሳሪያዎቻችን ጸሎት፣ እምነት፣ እና የእግዚአብሔር ቃል ናቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሰይጣንን ማሸነፍ እንድንችል ብርታትና ኃይል ይሰጠናል፡፡

**ኤፌሶን 6:10:11** «በተረፈ በጌታና ብርቱ በሆነው ኃይሉ ጠንክሩ፡፡ የዲያቢሎስን የተንኮል ስራ መደምሰስ ትችሉ ዘንድ የእግዚአብሔር ሙሉ የጦር እቃ ልበሱ፡፡»

### የቤተ ክርስቲያን ድል

በዘመናት ሁሉ ስደት ቤተ ክርስቲያንን እንድትጠነክር እንድታድግ አድርጓል፡፡ ከኃጢአት እና ከሐሰት ትምህርቶች ያድናት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ የመነቃቃት ማዕበልን ልኳል፡፡ አሁን መከራ ሊደርስብዎ ይችላል፤ ነገር ግን ጦርነቱ በቅርብ ጊዜ ይጠናቀቃል፡፡ ሰይጣን ይሸነፋል ቤተክርስቲያንም ለዘላለም ከክርስቶስ ጋር ትነግሳለች፡፡

**ማቴዎች 16:18** «ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ፣ የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም፡፡»

**ሮሜ 8:37** «በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን፡፡»

## በዚህ ሁሉ የእርስዎ ድርሻ

በዚህ ጦርነት ዉስጥ እያንዳንዱ ክርስቲያን ወታደር ነው።

> **2 ጢሞ 2፡3** «እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ በጎ ወታደር ከእኛ ጋር መከራን ተቀበል።»
>
> ***ራይዕ* 2፡10** «ሊደርስብህ ያለውን መከራ አትፍራ እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ሁን እኔም የህይወትህ አክሊል እሰጥሃለሁ።»

| **የሚከተለውን ይስሩ** |
|---|
| 1 እያንዳንዱ ክርስቲያን እየተካሄደ ባለው መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ያለ ወታደር ነው። ምክንያቱም እያንዳንዱ ክርስቲያን የ ……………………ኢላማ ነው። |
| 2 ክርስቲያን የሆነ ሰዉ ሰይጣንንና ዉሸቱን ማሸነፍ የሚችለዉ የእዉነት ሰይፍ የሆነዉን..........................በመበጠቀም ነዉ። |

## <u>ይህን ኮርስ በማጠናቀቅዎ እንኳን ደስ አለዎ!</u>

አሁን የክፍለ ትምህርት 6ን ጥያቄዎች በዚህ መፅሐፍ መጨረሻ ላይ ከሰሩ በኋላ አጠቃላይ መልሶችዎን በአቅራቢያዎ ለሚገኘዉ ጽህፈት ቤታችን ይላኩልን።

*ይህን ኮርስ በማጥናትዎ እንደተደሰቱ ተስፋ እናደርጋለን። ሌሎች ኮርሶችንም በመዉሰድ እግዚአብሔር ለሕይወትዎ ያለዉን ዕቅድ የበለጠ እንዲረዱ ይበርቱ እንላለን።*

## <u>እግዚአብሔር ይባርክዎ!</u>

# <u>የትምህርቶች መከለሻ ጥያቄዎች</u>

## *መመሪያዎች*

| *ግልፅ አድርገዉ ይፃፉ!* |
|---|

ስም………………………………………………………………………………………….

ፖ. ሳ .ቁ………………………………………………………………………………………

የመኖሪያ ቤት አድራሻ…………………………………………………………………….

የሚኖሩበት ከተማ………………………………………………………………………….

ስቴት/ክፍለ ግዛት………………………የፓስታ/የመኖሪያ አካባቢ ኮድ…………….

አገር…………………………………………………………………………………………

የኢሜይል አድራሻ…………………………………………………………………….

የሕይወት ዓበይት ጥያቄዎችን አጠናቀዉ ሰርቲፊኬት ለማግኘት ከዚህ ቀጥሎ የሚገኙትን ጥያቄዎች በሙሉ ይመልሱ

መልስ የሰጡባቸዉን ገጾች፣ የጓደኞችዎን ስምና አድራሻ ከያዘዉ ገፅ ጋር በጥንቃቄ ለይተዉ በማዉጣት በአቅራቢያዎ ለሚገኘዉ የግሎባል ዩኒቨርሲቲ ጽሕፈት ቤት ይላኩ።

*አሁን ከትምህርት 1-6 ላሉት ትምህርቶች የመከለሻ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተዘጋጅተዋል።*

*<u>የቻሉትን ያህል ለሁሉም ጥያቄዎች መልሳቸዉን ይስጡ።</u>*

# ትምህርት 1

1. በትምህርት 1 ዉስጥ ይህን ይስሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሻለሁ በቃል የሚያዙ ጥቅሶችንም አጥንቻለሁ:: ☐አዎ ☐አልሰራሁም
2. ስለ ሰዉ አፈጣጠርና ስለ ዓለም እዉነትን የምንማርበት ብቸኛዉ መንገድ ........................................................ ነዉ::
3. እግዚአብሔር ሰዉንና ዓለምን የፈጠረዉ ለ............................................................ ነዉ::
4. በሽታና ሞት ወደ ዓለም የመጡትበት ምክንያት_........................................................
5. በሐጢያታችን ምክንያት ሊመጣብን የነበረዉ ቅጣት የተወገደልን በ ........................................................ ነዉ::

# ትምህርት 2

1. በትምህርት 2 ዉስጥ ይህን ይስሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሻለሁ በቃል የሚያዙ ጥቅሶችንም አጥንቻለሁ:: ☐አዎ ☐አልሰራሁም
2. ስለ እግዚአብሔር እዉነቱን ማወቅ ያለብኝ እርሱ የእኔ............................................... እና........................................................ ስለሆነ ነዉ::
3. እግዚአብሔር በቃሉ ስለራሱ ከተናገረዉ ነገር ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ይችላሉ:: እንዲሁም ከግልዎ........................................................ ሰለ እርሱ ማወቅ ይችላሉ::
4. እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ነዉ:: ሁሉን ያዉቃል እንዲሁም ………………………… ማድረግ ይችላል::
5. ለእርሱ ስላለዎ አምልኮ እግዚአብሔር እዉነተኛና ታማኝ እንዲሆኑለት ይፈልጋል እንዲሁም ስለ........................................................ እንዲያመሰግኑት ይፈልጋል::

# ትምህርት 3

1. በትምህርት 3 ዉስጥ ይህን ይስሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሻለሁ በቃል የሚያዙ ጥቅሶችንም አጥንቻለሁ:: ☐አዎ ☐አልሰራሁም
2. እኔና እርስዎ የተወለድነዉ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆንና የእርሱን መልክ........................................................ነዉ::
3. ሰዉ ስለሆንኩ በጎዉን ከክፉ ለይቼ ማወቅ፣ ዉበትን ማድነቅ፣ ማሰብ ፣እግዚአብሔርን ማምለክና ጠቃሚ ነገሮችን መስራት እችላለሁ:: እነዚህ ሁሉ የሚያሳዩት በዉስጤ …………………………መኖሩን ነዉ::
4. ክፉ ነገሮችን የማደርግና የስጋየን ፍላጎት ብቻ ለማርካት ብቻ መኖሬ በዉስጤ ያለዉ የእግዚያብሔር መልክ ........................................................ መሆኑን ያሳያል::
5. እግዚአብሔርን ለማስደሰት ባህሪየን እርሱ ........................................................ እና በዉስጤ የእርሱን መልክ........................................................ መፍቀድ አለብኝ::
6. ኢየሱስን አዳኜ አድርጌ ስቀበል የእግዚአብሔር ልጅ እሆናለሁ የእርሱ አምሳል በዉስጤ ይመለሳል:: ይህ መሆኑን እግዚአብሔር የሚያሳየኝ በ............................፣በ............................ ምስክርነትና በ............................አማካኝነትና ነዉ::

## ትምህርት 4

1. በትምህርት 4 ውስጥ ይህን ይስሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሻለሁ በቃል የሚያዙ ጥቅሶችንም አጥንቻለሁ፡፡ ☐አዎ ☐አልሰራሁም
2. ከሁሉ በላይ የሆነውን ፍላጎት ያሟላን ሰው የሚገልፁ ሐሳቦች ላይ ያስምሩ
   ማርታ መንፈሳዊ ሕይወትን ከእግዚአብሔር ተቀብላለች
   ዮናስ ከዕውርነት ተፈውሶአል
   ቶማስ ብዙ ገንዘብ የሚያገኝበትን መንገድ አግኝቶአል
   ከበደ እየሱስ ክርስቲስ አዳኙ እንዲሆን ጠየቀ
3.ትልቁ ኃጢያት የእዚአብሔር ዋና ትዕዛዝ የሆነዉን.....................................ነው
   ይኸዉም እግዚአብሔርን .....................................ነው፡፡
4. ኢየሱስ ክርስቶስ ያድነኝ ዘንድ ለመጠየቅ የተሻለዉ ጊዜ .....................................ነው፡፡
5. የመጀመሪያዉን ስፍራ ለ .....................................ከሰጠሁ የምለብሰዉንና የምበላዉን እግዚአብሔር እንደሚሰጠኝ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡

## ትምህርት 5

1.በትምህርት 5 ውስጥ ይህን ይስሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሻለሁ በቃል የሚያዙ ጥቅሶችንም አጥንቻለሁ፡፡ ☐አዎ ☐አልሰራሁም
2.የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሰው በሚሞትበት ጊዜ መንፈሱ ወደ ........................ይሄዳል፡፡
3.ኢየሱስ ወደ ምድር ተመልሶ ሲመጣ የእርሱ የሆኑት ሁሉ እንደ ........................የሆነ አካል ይሰጣቸዋል፡፡
4. ምንግስተ ሰማይ እግዚአብሔር ለ........................ሁሉ ያዘጋጀው ስፍራ ነው፡፡ ሲኦል ደግሞ እግዚአብሔር ለሰይጣንና ለ........................ያዘጋጀው ነው፡፡
5. ያለብኝን ........................ለእግዚአብሔር ከተናገርኩና ........................አዳኜ አድርጌ ከተቀበልኩ የመንግስተሰማይን መንገድ መርጫለሁ፡፡

## ትምህርት 6

1. በትምህርት 6 ውስጥ ይህን ይስሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሻለሁ በቃል የሚያዙ ጥቅሶችንም አጥንቻለሁ፡፡ ☐አዎ ☐አልሰራሁም
2. የእዉነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑ ሰዎች........................ን መሪያቸው አድርገው የሚከተሉ ናቸው፡፡
3. እዉነተኛ ቤተ ክርስቲያን አራት ዋና ዋና ነገሮችን ታደርጋለች፡፡ የሚከተሉትን ሐሳቦች በመሙላት እነዚህን ነገሮች ግለፅ፡
   እዉነተኛ ቤተ ክርስቲያን ........................ታመልካለች፣ ስለኢየሱስ ........................ትናገራለች፣ ለምዕመናን ........................ታስተምራለች፣ እንዲሁም ........................ለሆኑት እንክብካቤ ታደርጋለች፡፡
4. የእዉነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑት ........................በማድረግ እርስ በርስ በመንፈሳዊ ህይወታቸው ለማደግ ይረዳዳሉ፡፡
5. እዉነተኛ ቤተ ክርስቲያን የሚኖራት የድል ዓይነት የ........................ን ሙሉ በሙሉ መሸነፍ ያካትታል፡፡

# <u>አስተያየቶችና ጥያቄዎች</u>

**ምናልባት የግል አስተያየትዎን መግለፅ ይፈልጉ ይሆናል ያ ከሆነ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ።**

1.ትምህርት 1ን ከመጀመርዎ በፊት የእግዚአብሔርን ዕቅድ ተረድተዉ ኢየሱስን አዳኝዎ አድርገዉ ተቀብለዉ ነበር? አዎ/አይ

2.ያልተቀበሉ ከነበሩ እነዚህን ትመህርቶች ከተማሩ በኋላ ተቀበሉ? አዎ/አይ

3.እስካሁን ካልተቀበሉት አሁን ሊቀበሉት ይፈልጋሉ? አዎ/አይ

4.የሚሄዱበት ቤተ ክርሲያን አለዎ? አዎ/አይ
ክሆነ የትኛዋ ቤተ ክርስቲያን?

5.በአካባቢዎ የሚገኝ የቤተ ክርስቲያን አድራሻ ማግኘት ይፈልጋሉ? አዎ/አይ

6.እነዚህ ተምህርቶች ስለ እግዚአብሔር ብዙ እዉነቶችን አካትተዋል አሁን በህይወትዎ ከሁሉ በላይ የረዳዎት የትኛ ነዉ?

............................................................................................................
..................................................................................................................
..................................................................................................................
..................................................................................................................
....

7.ጸሎት የሚፈልጉ ከሆነ ክርስቲያን ወንደሞችና እህቶች እንዲፀልዩልዎት ያለዎትን የፀሎት ጥያቄ ይፃፉ

………………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………

8.እነዲህ ዓይነት ሌሎች ኮርሶችን ለመከታተል ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይፈልጋሉ? አዎ/አይ

ይህን ኮርስ ስላጠናቀቁ እንኩአን ደስ አለዎ!

## እግዚአብሔር ይባርክዎ።

*የጓደኞችዎን ስምና አድራሻ ቢልኩልን ከ«የሕይወት አበይት ጥያቄዎች»ትምህርት 1ን እንልክላቸዋለን፡፡*

## ግልፅ አድርገው ይፃፉ

ስም......................................................................................................
ፖ. ሳ .ቁ.....................................................................................................
የመኖሪያ ቤት አድራሻ.....................................................................................
የሚኖሩበት ከተማ............................................................................................
ስቴት/ክፍለ ግዛት..........................የፓስታ/የመኖሪያ አካባቢ ኮድ...............
አገር.......................................................................................................

ስም......................................................................................................
ፖ. ሳ .ቁ.....................................................................................................
የመኖሪያ ቤት አድራሻ.....................................................................................
የሚኖሩበት ከተማ............................................................................................
ስቴት/ክፍለ ግዛት..........................የፓስታ/የመኖሪያ አካባቢ ኮድ...............
አገር.......................................................................................................

ስም......................................................................................................
ፖ. ሳ .ቁ.....................................................................................................
የመኖሪያ ቤት አድራሻ.....................................................................................
የሚኖሩበት ከተማ............................................................................................
ስቴት/ክፍለ ግዛት..........................የፓስታ/የመኖሪያ አካባቢ ኮድ...............
አገር.......................................................................................................

ስም......................................................................................................
ፖ. ሳ .ቁ.....................................................................................................
የመኖሪያ ቤት አድራሻ.....................................................................................
የሚኖሩበት ከተማ............................................................................................
ስቴት/ክፍለ ግዛት..........................የፓስታ/የመኖሪያ አካባቢ ኮድ...............
አገር.......................................................................................................